## የጃኑዋሪ 2018 QuickNotes ቁጥር 1

**የ2019 በጀት ዓመት የስራ ማስኬጃ በጀት፡- ይበልጥ ግንዛቤ ያግኙ፣ አስተዋጾ ያድርጉ፡-**

**ተሳትፎ ያድርጉ እና ሃሳብዎን ይግለጹልን! ስለ MCPS የሥራ ማስኬጃ በጀት አስተያየትዎን ለመግለጽ ይህ እድል አያምልጥዎት።**

ዲሴምበር 19 የት/ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ/ Superintendent Jack Smith የ$2.59 ቢሊዮን ለ 2019 የበጀት ዓመት ሥራ ማስኬጃ እቅድ አቅርበዋል። MCPS ስለ በጀቱ ያለዎትን አስተሳሰብና አስተያየት መስማት ይፈልጋል። ወላጆች፣ ተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባሎች በጀቱን እንዲገነዘቡና ለበጀቱ ምደባ እገዛ እንዲያደርጉ ዲስትሪክቱ ስልቶችን ፈጥሯል። እነዚህ ስልቶች በበ MCPS የጀት ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ።

ስለ MCPS የሥራ ማስኬጃ በጀት መመደብ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳሰብ ከሞንጎመሪ ካውንቲ ተመራጭ ባለስልጣኖቻችን ጋር ለሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ለካውንቲው የሥራ ሃላፊዎችእና ለሞንጎመሪ ካውንቲ ካውንስል —በኢ-ሜይሎች፣ በደብዳቤዎች፣ እና ምስክርነት በመስጠት የእርስዎን አመለካከትና አስተያየትዎን ማካፈል እንዳለብዎት እርግጠኛ ይሁኑ። ጃኑዋሪ 4 እና 10 በ 6:30 p.m የትምህርት ቦርድ የሕዝብ አስተያየቶችን ይቀበላል። ቦርዱ በበጀት ጉዳዮች ላይ ስራውን የሚጀምረው ጃኑዋሪ 18 እና 25 በ 5 p.m ላይ ሲሆን ፌብሯሪ 13 በሚኖረው ስብሰባ የበጀት እርምጃ እንደሚወስድ ይጠበቃል።

ለትምህርት ቦርድ ምስክርነት ስለመስጠት የበለጠ መረጃ በዚህ ድረ-ገጽ ለማግኘት ይቻላል። http://www.montgomeryschoolsmd.org/boe/community/participation.aspx

ሌሎች መገልገያዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-

## የሥራ ማስኬጃ በጀት ድረ-ገጽ

የበጀት ዓመት 2019 በራሪ ወረቀት
http://www.montgomeryschoolsmd.org/uploadedFiles/departments/budget/fy2019/MCPS-Budget-Flyer-2019-12-18-17-FINAL.pdf

የት/ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ/Superintendent Jack Smith ያቀረቡትን የበጀት ዕቅድ እዚህ ይመልከቱ፡-
http://mcpsmd.swagit.com/play/12192017-1991

የኮሌጅ እና የሥራ ዝግጁነት ምሽት ጃኑዋሪ 17 ይካሄዳል።

ይህ ዝግጅት የሚመለከተው ከ6ኛ - 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን እና ወላጆቻቸውን ሲሆን የሚካሄደው በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-(Gaithersburg High School) ነው።

ከ6ኛ -12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ረቡዕ ጃኑዋሪ 17 በሚካሄደው "ለስኬታማነት በቅድሚያ ማቀድ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ የኮሌጅ እና የሥራ ዝግጁነት ምሽት እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። ቀደም ሲል ይህ ዝግጅት ታቅዶ የነበረው ለጃኑዋሪ 11 እንደሚካሄድ ነበር። በ MCPS እና Montgomery County Council of PTAs ትብብር የሚካሄደው ይህ ዝግጅት ለኮሌጅ እና ለሥራ እንዴት ጥሩ ዝግጅት ለማድረግ እንደሚቻል ትምህርት ለማግኘት እድል ይሰጣል። MCPS የሚሰጣቸውን እድሎችና ግብአቶች/መገልገያዎች/resources መዳሰስ እና ወቅቶችን ለይቶ ማወቅ፣ ከ MCPS የቀድሞ ምሩቃን ያላቸውን ልምዶች ማዳመጥ፣ እና ሌሎችም።

ዝግጅቱ የሚካሄደው ከ 6:30–8:45 p.m. ጃኑዋሪ 17 በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Gaithersburg High School)፣ 101 Education Blvd in Gaithersburg ነው። የበረዶ ቀን ጃኑዋሪ 25 ነው።

ለምዝገባ (RSVP here) ይህንን ድረ-ገጽ ይመልከቱ፡-

**በትምህርት ገበታ ላይ ስለ ትክክለኛነት/ሚዛናዊነት ጃኑዋሪ 27 ውይይት ይካሄዳል።**

በዚህ ዝግጅት ላይ ውይይቱ የሚመለከታቸው የትምህርት ባለሚሎች፣ የቢዝነስ እና የመንግስት ባለሥልጣናት የሚሳተፉበት ሲሆን አቅራቢው የጆርጅ ቢ. ቶማስ፣ ሲኒየር ትምህርት አካደሚ/George B. Thomas, Sr. Learning Academy ነው።

ቅዳሜ ጃኑዋሪ 27፣ በ Universities at Shady Grove in Rockville በሞንጎመሪ ካውንቲ ስለትምህርት ውይይት ይካሄዳል። በትምህርት ገበታ ላይ ስለ ትክክለኛነት/ሚዛናዊነት ውይይት የሚቀርበው በጆርጅ ቢ. ቶማስ፣ ሲኒየር ትምህርት አካደሚ/George B. Thomas, Sr. Learning Academy ሲሆን የትምህርት ባለሚሎችን፣ የመንግስት ባለሥልጣናትን እና የቢዝነስ ባለቤቶች/ሃላፊዎችን ጭምር ያሳትፋል።

በተናጋሪነት የተጋበዙት እንግዶች Princess Moss, secretary-treasurer of the National Education Association/የአገር አቀፍ ትምህርት ማህበር ጸሐፊ-በጅሮንድ፣ እና Dr. DeRionne Pollard, the president of Montgomery College/የሞንጎመሪ ኮሌጅ ፕሬዚደንት ናቸው። ሌሎች ንግግር የሚያደርጉ እንግዶች የሞንጎመሪ ካውንቲ ት/ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ጃክ ስሚዝ/MCPS Superintendent Jack Smith ፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ ዋና አስተዳዳሪ አይዛያህ ሌገት/Montgomery County Executive Isiah Leggett፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ የካውንስል አባል ክሬግ ራይስ/Montgomery County Councilmember Craig Rice እና የፔፕኮ ኮርፖሬት ምክትል

ፕሬዚደንት ደቢ ጃርቪስ/Vice President of Corporate Relations for Pepco Holdings Debbi Jarvis ናቸው።

ዝግጅቱ የሚካሄደው 8:30–11:30 a.m (ከቁርስ ጋር እና 8:30–9:30 a.m ኔትዎርክ ይኖራል) ክፍያ $40 ለአንድ ሰው። የክፍያ-ድጋፍ/Sponsorship እድል ይኖራል።

የጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲንየር የትምህርት አካደሚ/George B. Thomas, Sr. Learning Academy ልዩ ፕሮግራም ስለ ቅዳሜ ትምህርት ቤት ነው፣ በሞንጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ከሙዋዕለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል/K–12 በ12 ቦታዎች ላይ ተመጣጣኝ የትምህርት ድጋፍ እና የማስጠናት አገልግሎት ይሰጣል።

ስለ ዝግጅቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ በስልክ ቁጥር 301-287-8980 ይደውሉ ወይም በዚህ የቅዳሜ ት/ቤት ድረ-ገጽ ላይ ይመልከቱ። http://www.saturdayschool.org/

በትምህርት ገበታ ላይ ስለ ትክክለኛነት/ሚዛናዊነት ውይይት በራሪ ወረቀት PDF ይመልከቱ።

**የሁለተኛ ዓመት Comic Convention ተዘጋጅቷል።**

ቅዳሜ ጃኑዋሪ 27 MoComCon በሲልቨር ስፐሪንግ ቤተመጻሕፍት/Silver Spring Library ይካሄዳል። በነፃ ለመከታተል እንዲቻል ለሕዝብ ክፍት ሲሆን፣ በዚህ ዝግጅት ላይ የሚቀርቡ ዎርክሾፖች፣ ፕሮግራሞች፣ የሚታዩ እና የማስመሰል/cosplay እድሎች ናቸው።

የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት/ላይብራሪ ሁለተኛውን (MCPL) comic convention፣ MoComCon ጃኑዋሪ 27 ከ 11 a.m.–4 p.m በ Silver Spring Library, 900 Wayne Avenue in Silver Spring ያካሂዳል። የበረዶ ቀን ፌብሯሪ 10

ዝግጅቱ ነፃና ለሁሉም ክፍት ሲሆን፣በሳል ልምድ ያላቸዉ የኩምክና ጉባዔ ተሳታፊዎች፣ ጀማሪዎች፣ እና በሁሉም የእድሜ ደረጃ የሚገኙ ጉጉት ያላቸውን ያካትታል። ዝግጅቱ የተለያዩ ተወያይ ስብስቦችን/ፓነሎች፣ ዎርክሾፖች፣ ፕሮግራሞች፣ ትእይንቶች፣ ኤግዚቢሽን ለሚያሳዩና የማስመሰል/cosplay እድሎችን ያካትታል። እዚህ ድህረ-ገጽ ላይ የበለጠ መረጃ ይገኛል።
http://montgomerycountymd.gov/library/programs/mocomcon/

ዝግጅቶቹ የሚያካትቱት:-

- Superhero Storytime at 10:30 a.m.
- Light Wands with FutureMakers (ለሁሉም የዕድሜ ክልል ይሆናል)
- Introduction to Illustration with Jason Bunyan (ለወጣት ልጆች)
- አቅራቢዎች:- Marc Tyler Nobleman, Matthew Winner, እና local authors panel
- Harry Potter themed Escape Room
- DIY Dragon Eggs
- Cosplay contest with prizes (for children, teens and adults)

እስከ MoComCon ድረስ በጃኑዋሪ ውስጥ የሚካሄዱ በርካታ ሌሎች ዝግጅቶችም ይኖራሉ። እዚህ ይመልከቷቸው:-
ከ PDF ይመልከቱ:-

"መከባበር ይመረጣል" Video PSA የተወዳዳሪዎች ምዝገባ እየተካሄደ ነው።

በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት ከ6ኛ -12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ወጣት ልጆች በወጣት ፍቅረኛሞች መካከል ስለሚፈጸም ጥቃት እና የቤት ውስጥ ጠብና ጭቅጭቆችን በሚመለከት ትምህርት ሰጪ የሆነ ኦርጅናል ቪድዮ የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም ሰርተው እንዲያቀርቡ መፎካከሪያ ነው።

ዘጠነኛው ዓመታዊ መከባበር ይመረጣል ሞንትጎመሪ ቪዲዮ PSA / 9th Annual Choose Respect Montgomery video PSA ውድድር አሁን ተወዳዳሪዎችን ለመቀበል ክፍት ነው። በዚህ ውድድር ወጣት ልጆች ስለ ህዝባዊ አገልግሎት ኦርጅናል ቪዲዮ ማስታወቂያ አዘጋጅተው ስለ ፍቅረኛ ወጣት ልጆች ጥቃት እና ስለ ወጣት ልጆች የቤት ውስጥ ጭቅጭቅና ጠብ ትምህርት ሰጪ/ግንዛቤ ለመስጠት የሚያስችል የፈጠራ ችሎታቸውን ተጠቅመው የሚጋፈጡት ነው። በውድድሩ ላይ ለመሳተፍ የሚችሉት ከ6ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ሲሆኑ በየግላቸው ወይም በቡድን ሆነው ለመወዳደር ይችላሉ። **የሚያቀርቡበት ቀነ-ገደብ ዓርብ ማርች 16/2018 ነው።** የአሸናፊዎቹ ዝርዝር "መከባበር ይመረጣል - ጤናማ የወጣቶች ፍቅር" ኤፕሪል 15/2018 ኮንፍራንስ ላይ ይነገራል። ተጨማሪ መረጃዎች እዚህ ይገኛሉ። http://www.montgomerycountymd.gov/fjc/chooserespect.html

**ጌትስበርግ የመጻሕፍት በዓል ዝግጅት፣ "የታናሹ ስኬት  የድርሰት ውድድር" ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ተከፍቷል።**

በሁለቱ የድርሰት ውድድሮች ላይ ለአሸናፊዎቹ በሺዎች የሚቆጠር የዶላር ሽልማት ይሰጣል። መወዳደሪያ ሥራዎችን ለማቅረብ የተሰጠው ቀነ-ገደብ ፌብሯሪ 22 እና ፌብሯሪ 23 ነው።

የ MCPS ተማሪዎች በሁለቱም የስነፅሁፍ ውድድሮች የመሳተፍ እድል አላቸው።

Gaithersburg Book Festival (የመጽሐፍት ትርኢት)

በተከታታይ ለሁለተኛ ዓመት፣ የጌትስበርግ የመጻሕፍት ትርኢት ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በራሳቸው ነፃነት ተመራምረው በአጭር የፈጠራ ድርሰት ውድድር እንዲሳተፉ እድል ተሰጥቷቸዋል። ለአንደኛ፣ ሁለተኛ፣ እና ሦስተኛ ደረጃ አሸናፊዎች የገንዘብ ሽልማት ይኖራል።

ለውድድር የሚያቀርቡት ከ1000 ቃላት የሚበልጥ መሆን የለበትም እና በኤሌክትሮኒክስ via በድረ-ገጽ ቅጽ ሐሙስ ፌብሯሪ 22/2018 ከእኩለ-ሌሊት በፊት መቅረብ አለበት። የተሟሉ ደንቦችና መመሪያዎች በድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ።

ለማጣሪያ ተወዳዳሪነት እስከ 12 ድርሰቶች ተመርጠው ከመጻህፍት ፌስቲቫሉ ቀን አስቀድሞ በጌትስበርግ ፌስቲቫል ድረ-ገጽ ላይ ይለጠፋሉ። ዝግጅቱ፣ በዓመታዊ የመጻህፍት፣ የደራሲያን የማንበብና መጻፍ ጥበብ፣ ቅዳሜ ሜይ 19/2018 በጌትስበርግ ከተማ አዳራሽ ይከበራል።

የታናሽ ስኬታማነት/Junior Achievement

የ2018 የታናሽ ስኬታማነት/Junior Achievement የድርሰት ውድድር ማመልከቻ ለመቀበል በይፋ ተከፍቷል። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እስከ ዓርብ ፌብሯሪ 23/2018 ማመልከቻ እና ከ 1,000-1,500 ቃላት ድርሰቶቻቸውን ለማቅረብ ይችላሉ።

የዘንድሮው ርእስ በርካታ ታዋቂ የንግድ ድርጅት መሥራቾችና አካሂያጆች ቢልጌትስ እና ማርክ ዙከርበርግን ጨምሮ፣ የኮሌጅ ዲግሪ ሳይጨርሱ ጥለው የወጡ ናቸው/“Several great entrepreneurs, including Bill Gates and Mark Zuckerberg, dropped out of college before getting their degrees. ለአንተ/ለአንቺ የወደፊት ስኬታማነት የኮሌጅ ትምህርት ምን ያህል አስፈላጊ ነው ብለህ/ብለሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ? /how important do you think a college education is to your future success?” የሚል ነው።

ድርሰቶቹ የሚገመገሙት በፈጠራ ችሎታ እና ኦርጅናል መሆናቸው፣ አሳማኝነት፣ ሰዋሰው እና የፊደላት አጠባበቅ፣ ቁምነገሩን የመረዳት/የመገንዘብ ብቃት፣ እና ለቀረበው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠቱ ላይ ነው። በዋነኛነት አሸናፊ የሆነ/ች $20,000 ይሸለማል/ትሸለማለች፣ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ እና ሦስተኛ ደረጃ አሸናፊ ለሆኑት $10,000 ሽልማት ይሰጣል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡- www.JAessay.org

**ደህንነትን ለመጠበቅ የወጣት ልጆች አልኮሆል መጠቀም ስለሚያስከትለው ጉዳት በመግለጽ ትምህርት የሚሰጥ የቪድዮ ውድድር፦**

ውድድሩ የተከፈተው ሁለት ወይም ከዚያ የበለጠ በቡድን ለሚወዳደሩ የመካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ነው። መወዳደሪያ ለመቀበል የሚቻለው ከጃኑዋሪ 22 እስከ ፌብሯሪ 2/ January 22–February 2 ነው።

ደህንነት መጠበቅ፦ ከሃያ-አንድ ዓመት በታች ከአልኮሆል መታቀብ ህብረት ዓመታዊውን ከ21 ዓመት እድሜ በታች አልኮል መጠጣት ስለሚያስከትለው ጉዳት/ጠንቅ የሚገልጽ የ30-ሴኮንድ የህብረተሰብ አገልግሎት መልእክት የቪድዮ ውድድርን ስፖንሰር ያደርጋል።

ውድድሩ የተዘጋጀው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሆነው ለሚወዳደሩ የሞንጎመሪ ካውንቲ የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ነው። ለአሸናፊ ቡድኖች ከ $100 እስከ $1,000 ሽልማት ተዘጋጅቶላቸዋል። **መወዳደሪያውን ከጃኑዋሪ 22 እስከ ፌብሯሪ 2 2018/January 22–February 2, 2018 ድረስ ለመቀበል ክፍት ይሆናል።**

ደህንነት መጠበቅ፦ ከሃያ-አንድ ዓመት እድሜ በታች የአልኮል ታቅቦ/መከልከል ህብረት ዋና ዓላማው ከሚፈቀድላቸው እድሜ በታች ያሉ አልኮል እንዳይጠቀሙ መከላከል፣ ታዳጊዎች አልኮል ከማግኘት እንዲታቀቡ/ለመቀነስ እና ከ21 ዓመት እድሜ በታች ያሉ ወጣቶች ላይ አልኮል የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ነው።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ስለ ውድድሩ ይፋ ህጎችን/ደንቦችን ለማወቅ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።
http://www.montgomerycountymd.gov/dlc/education/kis/coalition/

**ተማሪዎች እቤታቸው ለመጠቀም Microsoft Office በነፃ ለመጫን ይችላሉ።**

ተማሪዎች እስከ አምስት ድረስ መሳሪያዎች/ድቫይስ ላይ Microsoft Office suite of programs on up to five devices ለመጫን ይችላሉ።

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ እና Microsoft በገቡት የህብረት ስምምነት መሠረት ለተማሪዎች ወቅታዊውን Microsoft Office software suite, Office 365 ProPlus በነፃ ጭነው እንዲጠቀሙ ተፈቅዷል። Office 365 ProPlus እንደ Outlook፣ Word፣ Excel እና PowerPoint ያሉ ሙሉ የ Microsoft መተግበሪያዎችን፣ እንዲሁም የ Office ፋይሎችን በመስመር ላይ የመፍጠር፣ የማቆየት እና የማጋራት ችሎታዎችን ያካትታል። በፕሮግራሙ መሠረት ተማሪዎች እና ሠራተኞች Microsoft Office softwareን እስከ አምስት መገልገያዎቻቸው ላይ ያለምንም ክፍያ ለመጫን ይችላሉ። መገልገያዎቹም PCs, Macs, tablets ወይም ስልኮቻቸው ላይ ሊሆን ይችላል።

በተለያዩ ቋንቋዎች ለመጫን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና መመሪያዎች:-
www.montgomeryschoolsmd.org/parents/